Minnesota Department of Health

# ንቁ የነቀርሳ በሽታ

ምርመራዎ የነቀርሳ በሽታ እንዳለብዎት የሚያሳይ ከሆነ የሚከተሉትን ነጥቦች ማወቅ አለብዎት፦

- ነቀርሳ ኃይለኛ በሽታ ቢሆንም ትክክለኛው ሕክምናና መድሃኒት ከተወሰደበት **መዳን የሚችል** ነው።
- አንዳንድ ነቀርሳ የያዛቸው ሰዎች በሽታውን ለሌላ ሰው ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

## ነቀርሳ እንዴት ሊይዘኝ ቻለ?

ማንኛውም ሰው ነቀርሳ ሊይዘው ይችላል። የሳንባ ነቀርሳ የያዘው ሰው ሲስል፣ሲያስነጥስ ወይም ሲነጋገር የነቀርሳ ጀርሞች አየር ውስጥ ሊያሠራጩ ይችላሉ። ማንኛውም በቅርብ ያለ ሰው ጀርሞቹን ከአየር ጋር ወደ ውስጥ በመሳብ ሊያስገባ ይችላል። ነቀርሳ እጅ በመጨበጥ፣በምግብ፣በሰሃን፣ በጨርቅ ወይም በሌሎች ዕቃዎች አያስተላልፍም።



የነቀርሳ ጀርሞቹ ሰውነትዎ ውስጥ ሲገቡ ይደበቃሉ። እነዚህ የተደበቁ የነቀርሳ ጀርሞች ሰውነትዎን አይጎዱም፣ሊያሳምምዎትም አይችሉም። ይህ “ድብቅ ነቀርሳ” ወይም “LTBI” ተብሎ ይታወቃል። ድብቅ ነቀርሳ ለአጭር ጊዜ ወይም ለብዙ ዓመታት ሊቆይ ይችላል። ነቀርሳ ያመምዎት ጀርሞቹ ነቅተው ማደግና ሰውነትዎን መጉዳት ሲጀምሩ ነው። ይህ “የነቀርሳ በሽታ” ተብሎ ይታወቃል።

## የነቀርሳ በሽታ ሰውነቴን የሚጎዳው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

አብዛኛውን ጊዜ ነቀርሳ የሚጎዳው ሳንባዎትን ነው (የሳንባ ነቀርሳ)። ነቀርሳ ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን ሊጎዳ ይችላል።




ብዙ ጊዜ ነቀርሳ የሚገኝባቸው ቦታዎች

*(የሴሎች ማርጠብያና ማጽጃ ፈሳሽ የሚሠራ እጢ)

ነቀርሳ ያለባቸው ሰዎች ከሚከተሉት **ምልክቶች** አንድ ወይም ከዛ በላይ ሊኖርባቸው ይችላል፦

- 3 ሳምንት ወይም ከዛ በላይ የሚቆይ ሳል
- ክብደት መቀነስ
- ምግብ አልበላ ሲል
- ማታ ማታ ላብ
- ትኩሳት
- ብርድ ብርድ ሲል
- ድካም ወይም አቅም ማነስ
- ደረት ላይ ሕመም
- ሲስሉ ደም ወይም ቡና ዓይነት ቀለም ያለው ነገር ከሳንባ ሲወጣ

## ዶክተሮች ነቀርሳ መኖሩን እንዴት ነው የሚመረምሩት?

ለነቀርሳ በሽታ ከአንድ በላይ ምርመራ ሊያስፈልግ ይችላል፦

- **የማንቱ የቆዳ ምርመራ** አድርጎ ሰውነትዎ ውስጥ የነቀርሳ ጀርሞች መኖሩን ማወቅ ይቻላል - ጀርሞቹ የተደበቁ ቢሆኑም።
- **የደረት ራጅ** አንስቶ ጀርሞቹ ሳንባዎትን ጎድተው እንደሆነ ይታወቃል።
- **የአክታ ምርመራ** ማድረግ የነቀርሳ ጀርሞች ሳንባዎት ውስጥ እየተባዙ መሆኑን ያሳያል።

## እንዴት ሊሻለኝ ይችላል?

- ዶክተር ጋር ሄደው የነቀርሳ ጀርሞቹን የሚገድል ልዩ **የነቀርሳ መድሃኒቶች** መውሰድ አለብዎት።
- **የነቀርሳ ጀርሞች** ጠንካራ ሲሆኑ ለረጅም ጊዜ መኖር ይችላሉ። የነቀርሳ መድሃኒቶችን መውሰድ ከጀመሩ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ እየተሻልዎት ይመጣል። የነቀርሳ ጀርሞቹ በሙሉ መሞታቸውን ለማረጋገጥ መድሃኒቶቹን ቢያንስ ለ6 ወይም 9 ወር **መውሰድ መቀጠል** አለብዎት።
- ሕክምናዎን እስከሚጨርሱ ድረስ **ዶክተርዎን በየወሩ ማየት** አስፈላጊ ነው። ዶክተርዎም እየተሸልዎት መሆኑን ለማረጋገጥ ምርመራዎች ያደርጋል፣ መድሃኒትዎ ምንም ዓይነት ችግር እንዳላስከተለብዎት ይጠይቅዎታል እንዲሁም ለጥያቄዎችዎ መልስ ይሰጣል።

## መድሃኒቱን ባልወስድ ምን ይሆናል?

የነቀርሳ ጀርሞች በጣም ጠንካራ ናቸው። መድሃኒትዎን በትክክል ባይወስዱ እንደገና **ታመው ነቀርሳን ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላሉ።**

በደንብ ለመዳን **መድሃኒቶችዎን በሙሉ** ዶክተርዎ በሚነግርዎት መንገድ መውሰድ አለብዎት። መድሃኒትዎን በትክክል ካልወሰዱ ነቀርሳዎ ሊጠነክር ይችላል። ይበልጥ ጠንካራ የሆነ መድሃኒት ረዘም ላለ ጊዜ መውሰድ ይኖርብዎታል።

# የነቀርሳ በሽታ - ገጽ 2

## ዲኦቲ ምንድን ነው?

ዲኦቲ ማለት በጥብቅ ክትትል የሚደረግ ሕክምና ነው። ዲኦቲ መድሃኒትዎን እንዲወስዱ ያቃልላል። ዲኦቲ ማለት በየቀኑ መድሃኒትዎን በነርስ ወይም በጤና ጥበቃ ሠራተኛ ፊት ይወስዳሉ። ይህም የሚያስፈልግዎትን መድሃኒት በሙሉ እንደሚወስዱና ሕክምናው እየሠራ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል መንገድ ነው። መድሃኒትዎ አንድ ችግር ካስከተለ ወዲያው ሊታረም ይችላል።

**ዲኦቲ ነቀርሳን ያድናል!**

## ነቀርሳን ለሌላ ሰው ላስተላልፍ እችላለሁ?

ሳንባዎት ውስጥ ነቀርሳ ካለ ሌሎች ሰዎችን ከጀርሞችዎ ለመከላከል መጠንቀቅ አለብዎት። ነቀርሳው ሌላ የሰውነትዎ ክፍል ውስጥ ከሆነ የተገኘው የነቀርሳ ጀርሞቹ አብዛኛውን ጊዜ ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፉ አይችሉም።

የያዝዎት ነቀርሳ ወደ ሌላ ሰው መተላለፍ ይችል እንደሆን ለማወቅ ዶክተርዎን ወይም ነርስዎን ይጠይቁ። በቅርብዎት ያሉት ሰዎች እንዳይዛቸው ለመከላከል ምን ማድረግ እንዳለብዎት ይነግሩዎታል።

መድሃኒትዎን መውሰድ ከጀመሩ ከትንሽ ሳምንታት በኋላና ከተሻልዎት በኋላ የነቀርሳ ጀርሞቹ ወደ ሌላ ሰው አይተላለፉም። ዶክተርዎ መቼ ወደ ሥራ፣ት/ቤት ወይም ወደ ሌላ እንቅስቃሴዎች መመለስ እንደሚችሉ ይነግርዎታል።

## ስለ ነቀርሳ ሌላ ምን ማወቅ ይገባኛል?

- ዶክተርዎን ወይም ነርስዎን ከሚኔሶታ የጤና ክፍል በነጻ መድሃኒት እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይጠይቁ።
- ወደ ሌላ ስቴት ወይም ከተማ የመሄድ ዕቅድ ካልዎት ለዶክተርዎ ወይም ለነርስዎ ይንገሩ። ከሚሄዱበት ቦታ መድሃኒት እንዲያገኙ ይረዷዎታል።
- ነቀርሳ ካልዎት ዶክተርዎን የኤችአይቪ ምርመራ እንዲያደርግልዎት ይጠይቁ። ኤችአይቪ ያለባቸው ሰዎች ነቀርሳ በጠና ሊያሳምማቸው ይችላል። ኤችአይቪ ካለብዎት የተለዩ ዓይነት የነቀርሳ መድሃኒቶች ሊያስፈልግዎት ይችላል።

**ያስታውሱ ፡- ነቀርሳ የሚድን በሽታ ነዉ!**

## ስለ ነቀርሳ መድሃኒት ምን ማወቅ ያስፈልገኛል?

- የነቀርሳ መድሀኒቶች ባብዛኛው ምንም ችግር አያስከትሉም፣ ሆኖም አንዳንድ ሰዎች ላይ የሚከተሉትን ሊያስከትሉ ይችላሉ። **ከሚከተሉት ምልክቶች አንዱ ካለብዎት ዶክተርዎ ጋር ባስቸኳይ ይደውሉ ወይም ይሂዱ፡-**
  - ማስታወክ፣ የሆድ ሕመም
  - ምግብ አልበላ ሲል
  - ማቅለሽለሽ
  - ዓይን ወይም ቆዳ ቢጫ ሲሆን
  - የእጅ ወይም የእግር ጣት ሲጠዘጥዝ
  - አፍ ሲጠዘጥዝ ወይም ሲደነዝዝ
  - ዓይን ብዥ ሲል ወይም የማየት ችሎታ ሲቀየር
  - ጆሮ ውስጥ የመደወል ድምጽ ሲሰማ
  - መስማት ሲያስቸግር
  - ሲያዞር
  - መጋጠሚያ ላይ ሲያም
  - ከ3 ቀን በላይ የሚቆይ ትኩሳት
  - ቆዳ ሽፍ ሲል
  - መድማት ወይም በቀላሉ መቁሰል
- የነቀርሳ መድሃኒትዎትን በሙሉ በየቀኑ በተመሳሳይ ሰዓት ይውሰዱ።
- ዶክተርዎ አቁሙ እስከሚልዎት ድረስ የነቀርሳ መድሃኒትዎን መውሰድ ይቀጥሉ።
- የነቀርሳ መድሃኒት ሲወስዱ ቢራ፣ወይን ጠጅ ወይም ሌላ መጠጥ አይጠጡ።

**የክሊኒክዎ ዶክተር ወይም ነርስ ስም፡-**

____________________________________

____________________________________

**ስልክ ቁጥር:** (_____)______________________

**የነቀርሳ መድሃኒቶችዎ የሚከተሉት ናቸው:-**

___ አይሶናየዝድ (“INH”)
___ ሪፋምፒን
___ ፓይሪዛይነማይድ (“PZA”)
___ ኤታምብዩቶል
___ ቫይታሚን ቢ6
___ _______________
___ _______________

MINNESOTA MDH DEPARTMENT OF HEALTH
Tuberculosis Prevention and Control Program
P.O. Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-5414
1-877-676-5414
www.health.state.mn.us/tb

6/2005